እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ በሥራ ላይ ያለውን የኢንቨስትመንት ሕግ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፯፻፷፱/፪ሺ፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ "ኢንቨስትመንት" ማለት አዲስ ድርጅት ለማቋቋም ወይም ነባር ድርጅትን ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል በባለሀብት በገንዘብ ወይም በዓይነት ወይም በሁለቱም የሚደረግ የካፒታል ወጪ ነው፤

፪/ "ድርጅት" ማለት ለትርፍ የተቋቋመ ድርጅት ነው፤

፫/ "ካፒታል" ማለት የሀገር ውስጥ ወይም የውጭ ገንዘብ፣ የሚተላለፍ ሠነድ፣ የማምረቻ ወይም የአገልግሎት መስጫ መሣሪያ፣ ሕንፃ፣ የሥራ ማስኬጃ ካፒታል፣ የንብረት መብት፣ የፓተንት መብት ወይም ሌላ የንግድ ሀብት ነው፤

፬/ "ባለሀብት" ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ ኢንቨስት ያደረገ የአገር ውስጥ ወይም የውጭ ባለሀብት ነው፤

፭/ "የአገር ውስጥ ባለሀብት" ማለት የኢንቨስትመንት ካፒታል በሥራ ላይ ያዋለ ኢትዮጵያዊ ወይም አግባብ ባለው ሕግ እንደ አገር ውስጥ ባለሀብት የተቆጠረ የውጭ አገር ዜጋ ሲሆን መንግሥትንና የመንግሥት ልማት ድርጅትን እና አግባብ ባለው ሕግ የተቋቋመ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ይጨምራል፤

፮/ "የውጭ ባለሀብት" ማለት የውጭ ካፒታል ወደ ኢትዮጵያ በማስገባት ኢንቨስት ያደረገ የውጭ አገር ዜጋ ወይም ሙሉ በሙሉ በውጭ አገር ዜጋ ባለቤትነት የተያዘ ድርጅት ወይም ከአገር ውስጥ ባለሀብት ጋር በቅንጅት ኢትዮጵያ ውስጥ በተቋቋመ ድርጅት ኢንቨስት ያደረገ የውጭ አገር ዜጋ ወይም ድርጅት ሲሆን እንደውጭ ባለሀብት መቆጠር የፈለገ መደበኛ ነዋሪነቱ በውጭ አገር የሆነ ኢትዮጵያዊን ይጨምራል፤

WHEREAS, to these ends, it has become necessary to revise the existing law on investment;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## PART ONE
## GENERAL

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Investment Proclamation No. 769/2012".

### 2. Definitions

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1/ "investment" means expenditure of capital in cash or in kind or in both by an investor to establish a new enterprise or to expand or upgrade one that already exists;

2/ "enterprise" means an undertaking established for the purpose of profit making;

3/ "capital" means local or foreign currency, negotiable instruments, machinery or equipment, buildings, working capital, property rights, patent rights, or other business assets;

4/ "investor" means a domestic or a foreign investor having invested in Ethiopia;

5/ "domestic investor" means an Ethiopian national or a foreign national treated as a domestic investor as per the relevant law, and includes the government, public enterprises as well as cooperative societies established as per the relevant law;

6/ "foreign investor" means a foreigner or an enterprise wholly owned by foreign nationals, having invested foreign capital in Ethiopia or a foreigner or an Ethiopian incorporated enterprise owned by foreign nationals jointly investing with a domestic investor, and includes an Ethiopian permanently residing abroad and preferring treatment as a foreign investor;

፲፬/ "ኤጀንሲ" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የሚቋቋም የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ ነው፤

፲፭/ "ኢንቨስትመንት ቦርድ" ማለት የኤጀንሲው ከፍተኛ የአመራር አካል ነው፤

፲፮/ "አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት" ማለት ኤጀንሲው ወይም የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለመስጠት ሥልጣን የተሠጠው የክልል የኢንቨስትመንት አካል ነው፤

፲፯/ "የኢንዱስትሪ ልማት ቀጠና" ማለት የኢንዱስትሪ እድገትን፣ የአካባቢ ብክለት ተፅኖን የመቀነስ እና የከተሞች እድገትን በእቅድና በስርዓት የመምራት አበይት ዓላማዎችን የያዘ ሆኖ እቅድን መሠረት አድርጐ እንደመንገድ፣ የኤሌክትሪክ ሃይል፣ ውሃና የመሣሠሉ አስፈላጊ መሠረተ ልማቶች፣ የተለያዩ አገልግሎቶች ተሟልተውለት እና ልዩ የማበረታቻ ዐቅድ ኖሮት፣ አንድ ዓይነት ወይም ተመሣሣይነት ወይም ተመጋጋቢነት ያላቸው ኢንዱስትሪዎችን በስብስብ ለማልማት ወይም ሁለገብ ኢንዱስትሪዎችን ለማልማት የሚቋቋም ድንበር የተበጀለት አግባብ ባለው አካል የተሰየመ የተወሰነ ቦታ ነው፤

፲፰/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል፡፡

፫. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በማዕድንና ነዳጅ ፍለጋ፣ ምርመራና ማምረት ሥራዎች በሚደረግ ኢንቨስትመንት ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም፡፡

፬. <u>የሥልጣን ክልል</u>

፩/ የሚከተሉት ኢንቨስትመንቶች አስተዳደር በኤጀንሲው የሥልጣን ክልል ሥር ይወድቃሉ፡-

ሀ) ሙሉ በሙሉ በውጭ ባለሀብት የሚደረግ ኢንቨስትመንት፤

ለ) በአገር ውስጥና በውጭ ባለሀብቶች በቅንጅት የሚደረግ ኢንቨስትመንት፤

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፪(፭) መሠረት እንደ አገር ውስጥ ባለሀብት በተቆጠረ በትውልድ ኢትዮጵያዊ ባልሆነ የውጭ አገር ዜጋ የሚደረግ ኢንቨስትመንት፤

መ) የኢንቨስትመንት ማበረታቻ በሚሰጥበት የሥራ መስክ አግባብ ካለው የፌዴራሉ መንግሥት አካል የንግድ ሥራ ፈቃድ ማውጣት ባለበት የአገር ውስጥ ባለሀብት የሚደረግ ኢንቨስትመንት፡፡

14/ "Agency" means the Ethiopian Investment Agency to be established by regulation of the Council of Ministers;

15/ "Investment Board" means the highest governing body of the Agency;

16/ "appropriate investment organ" means the Agency or the executive organ of a region empowered to issue investment permits;

17/ "industrial development zone" means an area with distinct boundary designated by the appropriate organ to develop identical, similar and interrelated industries together or to develop multi-faceted industries based on a plan fulfilling infrastructures such as road, electric power and water and having incentive schemes with purposes containing industrial development, mitigating the impacts of environmental pollution and administering the development of urbans with plan and system;

18/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

3. <u>Scope of Application</u>

The provisions of this Proclamation may not be applicable to investments in the prospecting, exploration and development of minerals and petroleum resources.

4. <u>Jurisdiction</u>

1/ The administration of the following investments shall be under the jurisdiction of the Agency:

a) wholly foreign owned investment;

b) joint investment made by domestic and foreign investors;

c) investment made by a foreign national, not Ethiopian by origin, treated as a domestic investor pursuant to Article 2(5) of this Proclamation;

d) investment made, in areas eligible for incentives, by a domestic investor who is required to obtain a business license from the concerned federal organ.

፪/ አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት ከሚከተሉት ምክንያቶች አንዱን በተጨባጭ ሲያረጋግጥ የኢንቨስትመንት ፈቃዱን ሊሠርዝ ይችላል፡-

ሀ) ባለሀብቱ የኢንቨስትመንት ፈቃዱን ያገኘው በማታለል ወይም የሐሰት መረጃ ወይም መግለጫ በማቅረብ ከሆነ፤

ለ) የተሠጡት ማበረታቻዎች ከታቀደላቸው ዓላማ ውጭ ውለው ወይም ከሕግ ውጭ ለሌላ ሰው ተላልፈው ከተገኙ፤

ሐ) ባለሀብቱ ያለበቂ ምክንያት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ በተደነገገው መሠረት የኢንቨስትመንት ፈቃዱን ያላሳደሰ እንደሆነ፤

መ) ባለሀብቱ ስለፕሮጀክቱ አፈጻጸም በተከታታይ ለሁለት ጊዜ የሚጠበቅበትን ሪፖርት ያላቀረበ ከሆነ፤ ወይም

ሠ) የፕሮጀክቱ ትግበራ ተጀምሮ በጊዜው ካልተጠናቀቀ እና ኤጀንሲውም ፕሮጀክቱ እንደማይጠናቀቅ ሲያምንበት፡፡

፫/ አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚያደርገውን የኢንቨስትመንት ፈቃድ ስረዛ እርምጃ ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል፡፡ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰረዘበት ባለሀብት ፈቃዱ ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ ሲያገኝ የነበረው ጥቅም ወዲያውኑ ይቋረጥበታል፡፡

፬/ ፈቃዱ የተሠረዘበት ባለሀብት በማበረታቻነት ያገኛቸውን ጥቅሞች ፈቃዱ ከተሠረዘበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን እና አግባብነት ላላቸው ሌሎች አካላት ተመላሽ ያደርጋል፡፡

፭/ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ፈቃዱን ከሰጠው የኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት ውጭ በሌላ ማንኛውም አካል ሊታገድ ወይም ሊሠረዝ አይችልም፡፡

፮/ የኢንቨስትመንት ፈቃዱ የተሠረዘበት ባለሀብት ከአንድ ዓመት በፊት አዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማውጣት አይችልም፡፡

## ፳. ሪፖርት ስለማድረግና ስለመተባበር

የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያወጣ ማንኛውም ባለሀብት፡-

፩/ ስለኢንቨስትመንቱ የአፈጻጸም ሂደት በየሦስት ወሩ አግባብ ላለው የኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት ሪፖርት ማቅረብ፤ እና

2/ The appropriate investment organ may revoke an investment permit where it ascertains that:

a) the investor obtained the permit fraudulently or by submitting false information or statements;

b) incentives granted are misused or illegally transferred to another person;

c) the investor has failed, without good cause, to renew the permit in accordance with Article 17 of this Proclamation;

d) the investor fails to submit progress report of his project for two consecutive periods; or

e) the project can not commence operation with in the period and the Agency believes the project will not be operational.

3/ The appropriate investment organ shall notify the concerned institutions as to the measures of revocation taken in accordance with this Article. Upon revocation of an investment permit, the investor shall immediately lose entitlements to all benefits.

4/ An investor whose investment permit is revoked shall return, within one month as of the day of revocation, all the benefits granted to him to the Ethiopian Revenue and Customs Authority and other appropriate organs.

5/ An investment permit may not be suspended or revoked by any organ other than the appropriate investment organ having issued same.

6/ An investor whose investment permit is revoked may not be issued with a new investment permit before the lapse of one year from the date of revocation.

## 20. Duty to Report and Cooperate

Any investor with investment permit shall:

1/ submit progress reports on the implementation of his project to the appropriate investment organ at the end of every three months; and

፪/ አግባብ ባለው የኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት ሲጠየቅ ስለሚያካሂደው የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ መረጃ መስጠት፤

አለበት፡፡

ክፍል አምስት

የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነት እና የአገር ውስጥ ባለሀብት ከውጭ ኢንተርፕራይዝ ጋር ስለሚያደርገው የትብብር ስምምነት ምዝገባ

፳፩. ስለቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነት

፩/ ማንኛውም ባለሀብት ከኢንቨስትመንቱ ጋር በተያያዘ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነት በሚዋዋልበት ጊዜ ስምምነቱን ለኤጀንሲው በማቅረብ ማስመዝገብ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚቀርብ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነት ምዝገባ ጥያቄ የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርበታል፦

ሀ) በቴክኖሎጂ ተቀባዩ የተፈረመ የተሟላ የማመልከቻ ቅጽ፤

ለ) በቴክኖሎጂ ተቀባይና አቅራቢው መካከል የተደረገ የተረጋገጠ የስምምነት ሰነድ ፎቶ ኮፒ፤

ሐ) የቴክኖሎጂ ተቀባዩ የፀና የንግድ ሥራ ፈቃድ ወይም የኢንቨስትመንት ፈቃድ ፎቶ ኮፒ፤ እና

መ) የቴክኖሎጂ አቅራቢው የንግድ ምዝገባ ወይም የንግድ ሥራ ፈቃድ ማስረጃ፡፡

፫/ ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የምዝገባ ማመልከቻው ተሟልቶ ሲቀርብለት የምዝገባ ማስረጃውን ለባለሀብቱ ይሠጣል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ መሠረት በኤጀንሲው ያልተመዘገበ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነት ሕጋዊ ውጤት አይኖረውም፡፡

፭/ ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚያደርገውን የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነት ምዝገባ ለሚመለከታቸው የፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላት ያሳውቃል፡፡

2/ provide information concerning his investment activities whenever required by the appropriate investment organ.

## PART FIVE

## REGISTRATION OF TECHNOLOGY TRANSFER AND COLLABORATION AGREEMENTS WITH DOMESTIC INVESTERS

21. **Technology Transfer Agreement**

1/ Where any investor concludes a technology transfer agreement related to his investment, he shall submit same to the Agency for registration.

2/ An application for registration of a technology transfer agreement submitted in accordance with this Article shall fulfill the following:

a) a completed application form signed by the recipient of the technology;

b) a photocopy of the authenticated agreement between the recipient and provider of the technology;

c) a photocopy of a valid business license or investment permit of the recipient of the technology; and

d) a certificate of registration or business license of the provider of the technology.

3/ The Agency shall, upon receipt of a complete application for registration in accordance with sub-article (2) of this Article, issue a certificate of registration to the investor.

4/ A technology transfer agreement which is not registered with the Agency in accordance with this Article shall have no legal effect.

5/ The Agency shall notify the relevant federal executive organs the registration of technology transfer agreement made in accordance with this Article.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚወጣው ደንብ የሚሠጡትን ማበረታቻዎች ዓይነትና መጠን ይወስናል::

**፳፬. የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት ስለመሆን**

፩/ በፍትሐብሔር ሕግ ከአንቀፅ ፫፻፺ እስከ አንቀጽ ፫፻፺፫ የተደነገገው ቢኖርም የውጭ ባለሀብት ወይም እንደ አገር ውስጥ ባለሀብት የተቆጠረ የውጭ ዜጋ የመኖሪያ ቤትና ለኢንቨስትመንቱ ሥራ የሚያስፈልገው ንብረት ባለቤት ለመሆን ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ኢንቨስት ያደረጉትንም ባለሀብቶች ይጨምራል::

**፳፭. ስለኢንቨስትመንት ዋስትናና ጥበቃ**

፩/ ለኢንቨስትመንት የዋለ ሀብት ለሕዝብ ጥቅም ሲባልና በሕግ በተደነገገው መሠረት ካልሆነ በስተቀር ሊወሰድ ወይም ሊወረስ አይችልም::

፪/ ለኢንቨስትመንት የዋለ ሀብት ለሕዝብ ጥቅም ተብሎ ሲወሰድ ወይም ሲወረስ በወቅቱ የገበያ ዋጋ ተመጣጣኝ የሆነ ካሣ በቅድሚያ መከፈል አለበት::

፫/ ለዚህ አንቀፅ አላማ "መውረስ" የሚለው ቃል "መውሰድ" ከሚለው ጋር በተለዋዋጭነት በጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን እርምጃውም ተገቢ ወይም ተመጣጣኝ የካሳ ክፍያን ያስከትላል::

**፳፮. ገንዘብ ወደውጭ አገር ስለማዛወር**

፩/ ማንኛውም የውጭ ባለሀብት ከተፈቀደለት ኢንቨስትመንት ጋር በተያያዘ የሚከተሉትን ክፍያዎች በወቅቱ ባለው የምንዛሬ ተመን መሠረት በውጭ ምንዛሬ ከኢትዮጵያ ውጭ ለማዛወር ይችላል፡-

ሀ) ከኢንቨስትመንቱ ያገኘውን ትርፍና የትርፍ ድርሻ፤

ለ) ከውጭ አገር ላገኘው ብድር ዋና ገንዘብና ወለድ ክፍያ፤

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፩ መሠረት ካስመዘገበው የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነት ጋር የተያያዘ ክፍያ፤

2/ The regulation to be issued pursuant to sub-article (1) of this Article shall determine the type and extent of the entitlement to incentives.

**24. Ownership of Immovable Property**

1/ Notwithstanding the provisions from Article 390 to Article 393 of the Civil Code a foreign investor or a foreign national treated as domestic investor shall have the right to own a dwelling house and other immovable property requisite for his investment.

2/ The provisions of sub-article (1) of this Article shall also include those who have invested prior to the issuance of this Proclamation.

**25. Investment Guarantees and Protection**

1/ No investment may be expropriated or nationalized except for public interest and then, only in conformity with the requirements of the law.

2/ Adequate compensation, corresponding to the prevailing market value, shall be paid in advance in case of expropriation or nationalization of an investment for public interest.

3/ For the purpose of this Article the word "nationalization" shall be used interchangeably with the word "expropriation" and results in the payment of appropriate or adequate compensation.

**26. Remittance of Funds**

1/ Any foreign investor shall have the right, in respect of his approved investment, to make the following remittances out of Ethiopia in convertible foreign currency at the prevailing rate of exchange on the date of remittance:

a) profits and dividends accruing from the investment;

b) principal and interest payments on external loans;

c) payments related to a technology transfer agreement registered in accordance with Article 21 of this Proclamation;

መ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፪ መሠረት ካስመዘገበው የትብብር ስምምነት ጋር የተያያዘ ክፍያ፤

ሠ) አክስዮን ለአገር ውስጥ ባለሀብት ሲያዛውር ወይም ድርጅቱን በከፊል በአገር ውስጥ ባለሀብት ባለቤትነት ሥር ሲያደርግ ያገኘው ገንዘብ፤

ረ) ድርጅቱ ሲሸጥ ወይም ፈርሶ ሂሣቡ ሲጣራ የሚያገኘው ገቢ፤ እና

ሰ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፭(፪) መሠረት የሚፈጸም የካሣ ክፍያ::

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ቢኖርም በቅንጅት በተደረገ ኢንቨስትመንት ተሳታፊ የሆነ የአገር ውስጥ ባለሀብት ገንዘብ ወደ ውጭ ማዛወር አይፈቀድለትም::

፫/ በአንድ ድርጅት ውስጥ ተቀጥረው የሚሠሩ የውጭ አገር ዜጎች ካገኙት ደመወዝና ሌሎች ክፍያዎች የአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ወደ ውጭ አገር መላክ ይችላሉ::

## ክፍል ሰባት

## የኢንቨስትመንት አስተዳደር

### ፳፯. የኢንቨስትመንት አስተዳደር አካላት

የኢንቨስትመንት አስተዳደር አካላት ኤጀንሲውንና በክልል ሕጎች የሚወሰኑ የክልል ኢንቨስትመንት አካላትን ያጠቃልላል::

### ፳፰. የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር

ኤጀንሲው:-

፩/ የኢንቨስትመንት ጉዳዮችን በተመለከተ በማዕከልነት በማገልገል የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎችን ያበረታታል፤ ያስተባብራል፤ ያስፋፋል፤

፪/ ምቹና ተወዳዳሪ የኢንቨስትመንት ከባቢ እንዲኖር ለማድረግ የሚወሰዱ የፖሊሲና የአፈፃፀም ሀሳቦችን ያመነጫል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

d) payments related to a collaboration agreement registered in accordance with Article 22 of this Proclamation;

e) proceeds from the transfer of shares or of partial ownership of the enterprise to a domestic investor;

f) proceeds from the sale or liquidation of the enterprise; and

g) compensation paid to an investor pursuant to Article 25(2) of this Proclamation.

2/ Notwithstanding the provision of sub-article (1) of this Article, a local partner in a joint investment may not be allowed to remit funds out of Ethiopia.

3/ Expatriates employed in an enterprise may remit, in convertible foreign currency, salaries and other payments accruing from their employment in accordance with the foreign exchange laws of the country.

## PART SEVEN

## INVESTMENT ADMINISTRATION

### 27. Investment Administration Organs

The organs of investment administration comprise the Agency and regional investment organs to be defined by the laws of the respective regions.

### 28. Powers and Duties of the Agency

The Agency shall:

1/ serve as a nucleus for matters of investment and promote, coordinate and enhance activities thereon;

2/ initiate policy and implementation measures needed to create a conducive and competitive investment climate and follow up the implementation of same upon approval;

፫/ የውጭ ኢንቨስትመንቶች ሊመጡ ከሚችሉባቸው አገሮች ጋር አገሪቱ የምታደርጋቸውን የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ማስፋፊያና ጥበቃ ስምምነቶች ይደራደራል፣ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሲፈቀድም ይፈርማል፤

፬/ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ለማበረታታት እንዲሁም የአገሪቱን መልካም ገጽታ ለመገንባት የሚረዱ ጽሑፎችን እና ፊልሞችን ያዘጋጃል፣ ያሠራጫል፤ ዓውደ ርዕዮችን፣ ዓውደ ጥናቶችንና ሴሚናሮችን እንደአስፈላጊነቱ በአገር ውስጥና በውጭ አገር ያካሂዳል፤ በተዘጋጁ ተመሳሳይ ፕሮግራሞች ላይ ይሳተፋል፤ ሥልጠናዎችን ይሰጣል፤

፭/ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት በባለሀብቶች፣ በመንግሥታዊ መሥሪያ ቤቶች፣ በክልል መንግሥታትና በሌሎች ኢንቨስትመንትን በተመለከተ አግባብነት ባላቸው አካላት መካከል ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል፣ ያስተባብራል፤

፮/ ማናቸውንም ኢንቨስትመንት ነክ መረጃዎች ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ወቅታዊ ያደርጋል፣ ይተነትናል፣ ያሰራጫል፤

፯/ ተጨባጭ የኢንቨስትመንት ዕድል መግለጫዎችን በማዘጋጀት ያስተዋውቃል፣ ሲጠየቅም በቅንጅት ለሚደረግ ኢንቨስትመንት ተሳታፊዎችን የማገናኘት አገልግሎት ይሰጣል፤

፰/ በተሰጠው የሥልጣን ክልል መሠረት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሠርዛል፤ እንዲሁም የውጭ ባለሃብቶች ወደ አገር ውስጥ ያስገቡትን የኢንቨስትመንት ካፒታል ይመዘግባል፤

፱/ ከኢንቨስትመንት ጋር የተያያዙ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነቶችን ይመዘግባል፤

፲/ የውጭ ኢንተርፕራይዝ የሀብት መዋጮ ሳያደርግ ከወጪ ንግድ ጋር በተያያዘ ከአገር ውስጥ ባለሀብት ጋር የሚያደርገውን የትብብር ስምምነት ይመዘግባል፤

፲፩/ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሰጣቸውን ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ይከታተላል፣ የኢንቨስትመንት ፈቃዱ የያዛቸው ሁኔታዎች መከበራቸውንና ማበረታቻዎች ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤

3/ negotiate bilateral investment promotion and protection treaties with other countries where potential investment is likely to flow into the country and sign same upon approval by the Council of Ministers;

4/ prepare and distribute pamphlets, brochures, films and other materials, and organize such activities as exhibitions, workshops and seminars locally or abroad as may be appropriate, participate in similar activities and conduct trainings with a view to encourage and promote investment and build the image of the country;

5/ realize liaison and coordination between investors, public offices, regional governments and other relevant organs, with a view to enhancing investment;

6/ collect, compile, analyze, update and disseminate any investment related information;

7/ prepare and promote concrete investment opportunity profiles, provide upon request, match-making service of possible joint investment partners;

8/ issue, renew and cancel investment permits within its jurisdiction and register investment capital brought into the country by foreign investors;

9/ register technology transfer agreements related to investments;

10/ register export-oriented non-equity based collaboration agreements made between a domestic investor and a foreign enterprise;

11/ monitor the implementation of investment projects for which it has issued permits, ensure that the terms of the investment permit are complied with and incentives granted to investors are used for the intended purposes;

፲፪/ ለባለሀብቶች የመረጃ፣ የምክር እና የቴክኒክ ድጋፍ አገልግሎቶችን ይሰጣል፤ እንዲሁም የግብዓት ትስስር እንዲኖር መረጃ የማቅረብ ድጋፍ ይሰጣል፤

፲፫/ የድኅረ-ኢንቨስትመንት የድጋፍና ክትትል ሥራን ለዚህ ዓላማ ከተቋቋሙ አካላት ጋር ባቅንጅት ይሠራል፤

፲፬/ የክልል ኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤቶችን ለማጠናከር የሚረዱ የምክርና የቴክኒክ ድጋፎችን ይሰጣል፤ የጋራ የምክክር መድረኮችን ያዘጋጃል፤

፲፭/ ባለሀብቶች በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ይዘት ላይ የሚኖራቸው ግንዛቤ እንዲዳብር ያደርጋል፤

፲፮/ አግባብነት ካላቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር የኢንቨስትመንት ማነቆዎች እንዲፈቱ ያደርጋል፡፡

## ፳፱. የኢንቨስትመንት ቦርድ ሥልጣንና ተግባር

የኢንቨስትመንት ቦርድ፡-

፩/ የዚህን አዋጅ አፈፃፀምና የኤጀንሲውን ሥራዎች በበላይነት ይቆጣጠራል፤ ይከታተላል፤

፪/ ከዚህ አዋጅ አፈፃፀም ጋር ተያይዘው የሚነሱ የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤

፫/ እንደአስፈላጊነቱ ይህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ ደንቦች እንዲሻሻሉ ሃሳብ ያቀርባል፤

፬/ ይህን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል፤

፭/ የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር በሚሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኙ ባለሀብቶች በሚያቀርቡት ይግባኝ ላይ ይወስናል፤

፮/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሥራ ላይ ባለው ደንብ መሠረት ከሚፈቀደው የተለየ ወይም ተጨማሪ የሆነ ማበረታቻ እንዲሰጥ በሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲፈቀድ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤

12/ provide advisory service, information and technical support to investors and assist in the provision of information to ensure the existence of supply chains among investment projects;

13/ carry out post-investment support and monitoring services in collaboration with organs established for such purpose;

14/ provide advisory service and technical support which help strengthen regional investment organs; organize joint consultation forums;

15/ raise the awareness of investors on the contents of this Proclamation and regulations and directives issued hereunder;

16/ cause investment bottlenecks to be resolved in collaboration with appropriate government organs.

## 29. Powers and Duties of the Investment Board

The Investment Board shall:

1/ supervise and follow up the implementation of this Proclamation and the activities of the Agency;

2/ decide on policy issues arising in connection with the implementation of this Proclamation;

3/ recommend, as necessary, amendments to this Proclamation and regulations issued hereunder;

4/ issue directives necessary for the implementation of this Proclamation and regulations issued hereunder;

5/ decide on appeals submitted to it by investors against decisions of the Director General of the Agency;

6/ where necessary, forward recommendations, for approval by the Council of Ministers, to grant new or additional incentives other than what is provided for under existing regulation;

፬/ ኤጀንሲው ባለሀብቶችን ተክቶ የሚከተሉትን አገልግሎቶች ይሰጣል፡-

ሀ) ባለሀብቶች ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶቻቸው የሚውል መሬት ለማግኘት የሚያቀርቧቸውን ጥያቄዎች የማስፈጸም፤

ለ) የባለሀብቶችን የብድር አገልግሎት ጥያቄዎች የማስፈጸም፤

ሐ) የውጭ ባለሀብቶችን የመኖሪያ ፈቃድ ጥያቄዎች የማስፈጸም፤

መ) ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶቻቸው ላይ የተደረጉ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናቶች እንዲጸድቁ የሚያቀርቧቸውን ጥያቄዎች የማስፈጸም፤ እና

ሠ) ባለሀብቶች የውኃ፣ የኤሌክትሪክ ኃይልና የቴሌኮም አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚያቀርቧቸውን ጥያቄዎች የማስፈጸም፡፡

፭/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) አፈጻጸም የሚመለከታቸው የፌዴራል አስፈጻሚ አካላት ኤጀንሲው የሚያቀርበውን የባለሀብት ጥያቄዎች ተቀብለው በቅልጥፍና የሚያስተናግዱ የኢንቨስትመንት ዴስኮችን ማቋቋም ይኖርባቸዋል፡፡ የክልል አስፈፃሚ አካላትም ይህን አሰራር ተቀብለው የኢንቨስትመንት ዴስኮችን ማቋቋም ይችላሉ፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚመለከታቸው የፌዴራል ወይም የክልል አስፈጻሚ አካላት ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) የተመለከቱትን ኃላፊነቶች በአግባቡ እንዲወጣ አስፈላጊውን ሁሉ የመፈጸም ግዴታ አለባቸው፡፡

፯/ ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ማመልከቻው ተሟልቶ ሲቀርብለት ጉዳዩን አግባብ ካለው ሕግ አንፃር በመመርመር፡-

ሀ) ማመልከቻውን ከተቀበለው ተገቢውን ክፍያ በማስከፈል እና እንደ ሁኔታው ባለሀብቱ አግባብነት ያላቸውን የአገሪቱን ሕጎች ጠብቆ ለመሥራት ግዴታ እንዲገባ በማድረግ አስፈላጊውን ማስረጃ ይሰጣል፤ ወይም

ለ) ማመልከቻውን ካልተቀበለው ያልተቀበለበትን ምክንያት ለባለሀብቱ በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡

4/ The Agency shall provide the following services on behalf of investors:

a) execution of investors' requests for land required for their investment projects;

b) execution of investors' requests for loan;

c) execution of foreign investors' requests for residence permits;

d) execution of investors' requests for approval of environmental impact assessment studies conducted on their investment projects; and

e) execution of investors' requests to acquire water, electrical power and telecom services.

5/ For the implementation of sub-article (4) of this Article the appropriate federal executive organs shall establish investment desks that expedite and facilitate investors' requests submitted by the Agency. The regional executive organs may accept this practice and establish investment desks.

6/ Without prejudice to the provision of sub-article (5) of this Article, the appropriate federal or regional executive organs shall take measures necessary to help the Agency properly discharge its duties specified under sub-article (4) of this Article.

7/ Upon receipt of an application in accordance with sub-article (2) of this Article, the Agency shall, after examining the request in light of the relevant laws:

a) issue the necessary documents, upon receipt of the appropriate fee and causing the investor to enter an undertaking to observe the relevant laws of the country, where the application is found acceptable; or

b) notify the investor of its decision and the reason thereof in writing, where the application is found unacceptable.

፰/ ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከቱትን አገልግሎቶች ከሰጠ በኋላ ለአስፈላጊው ክትትል አግባብ ላላቸው የፌዴራልና የክልል አስፈጻሚ አካላት ያሳውቃል፡፡

፱/ የንግድ ሥራ ፈቃድ እንዲሰጠው ጥያቄውን ለኤጀንሲው የሚያቀርብ ባለሀብት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ማሟላት ያለበት ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው የፕሮጀክቱን አዋጪነት ጥናት ማቅረብ አለበት፡፡

፲/ የክልል የኢንቨስትመንት አካላት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለሰጧቸው ባለሀብቶች አግባብ ባላቸው የፌዴራልና የክልል መንግሥት ሕጎች መሠረት በዚህ አንቀጽ የተመለከቱትን የአንድ ማዕከል አገልግሎቶች ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

## ፴፩. ስለኢንቨስትመንት መረጃዎች

፩/ አግባብነት ያላቸው የፌዴራሉ መንግሥት ወይም የክልል መንግሥታት አካላት ኤጀንሲው ወይም የክልል ኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤቶች በዚህ አዋጅ የተሰጣቸውን ሥልጣንና ተግባር በአግባቡ መወጣት እንዲችሉ ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ስለሚውል መሬትና ወደ አገር ውስጥ ስለገባ የውጭ ካፒታል እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ፣ የተሟሉና ወቅታዊ ኢንቨስትመንት ነክ መረጃዎችን ለኤጀንሲውና ለክልል ኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤቶች ማስተላለፍ አለባቸው፡፡

፪/ እያንዳንዱ የክልል የኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት ስለክልሉ የሀብት ክምችትና የኢንቨስትመንት ዕድል የተጠናቀሩ መረጃዎችንና ስለክልሉ ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ የተዘጋጁ ሪፖርቶችን ለኤጀንሲው ያስተላልፋል፡፡

፫/ አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤ ት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ያገኛቸውን መረጃዎች ያጠናቅራል፣ ይተነትናል እንደ አስፈላጊነቱም ያሠራጫል፡፡

፬/ ማናቸውም የፌዴራል መንግሥት ወይም የክልል አስፈጻሚ አካል ኢንቨስትመንት ነክ መረጃዎችን አግባብ ባለው የኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት ሲጠየቅ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

## ፴፪. ስለአቤቱታ አቀራረብ

፩/ ማንኛውም ባለሀብት ከኢንቨስትመንቱ ጋር በተያያዘ ቅሬታ ካለው አግባብ ላለው የኢንቨስትመንት አካል አቤቱታ የማቅረብ መብት ይኖረዋል፡፡

8/ The Agency shall, after rendering the services provided for in sub-article (2) of this Article, notify the concerned federal and regional executive organs for the necessary follow up.

9/ Without prejudice to the requirements to be fulfilled in accordance with the relevant laws, an investor submitting his request to the Agency to be issued with a business license shall furnish his project feasibility study.

10/ Regional investment organs may give, to investors they have issued with investment permits, the one-stop shop services provided for in this Article, in accordance with the relevant federal and regional laws.

## 31. Investment Related Information

1/ The appropriate federal and regional executive organs shall transfer complete and updated information regarding land required for investment projects, investment capital brought into the country as well as other necessary investment related information to the Agency and regional investment organs in order to help them facilitate the proper discharge of their powers and duties under this Proclamation.

2/ Each regional investment organ shall transmit to the Agency information compiled with respect to the resource potential and investment opportunities of the region as well as periodic reports on investment activities therein.

3/ The appropriate investment organ shall compile, analyze and distribute, as necessary, the information it acquired pursuant to sub-article (2) of this Article.

4/ Any federal or regional executive organ shall have the duty to provide information relating to investment whenever so required by the appropriate investment organ.

## 32. Lodging of Complaints

1/ Any investor shall have the right to lodge complaints related to his investment with the appropriate investment organ.

ሐ) የተፈጥሮ ሀብቶችን፣ ቅርሶችን እና በሕግ የተለየ ጥበቃ እንዲደረግላቸው የተወሰኑ ቦታዎችን ለመንከባከብ፣

ሲባል በድርድር ወይም በውሳኔ ሊያዝ ይችላል።

**፴፭. የኢንዱስትሪ ልማት ቀጠናዎችን የሚመለከቱ ደንቦች**

፩/ በፌዴራሉ መንግስት በሚደረግ የኢንዱስትሪ ልማት ቀጠና የማልማት ስራ ላይ የሚሰማራ ተቋም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይቋቋማል።

፪/ የኢንዱስትሪ ልማት ቀጠናዎች ስለሚሰየሙበት አሠራር፣ ስለሚመደቡበት መሥፈርቶች፣ ስለድንበራቸው አወሳሰን፣ በቀጠናዎች ውስጥ ስለሚሠማሩ ባለሀብቶች መብትና ግዴታዎች፣ ከመንግስት ማግኘት ስለሚገባቸው ልዩ አገልግሎቶች አፈፃፀምና የቁጥጥር አሠራር፣ የሚያከናውኗቸው ግንባታዎች ስለሚፈፀሙበትና ቁጥጥር ስለሚደረግባቸው ሁኔታዎች፣ በዚህ አዋጅ ከሚያገኙት በተጨማሪነት ስለሚሰጣቸው ማበረታቻዎች እና በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉ ድንጋጌዎችን ለማስፈፀም አስፈላጊ ስለሆኑ ማናቸውም ጉዳዮች በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናሉ።

፫/ በዚህ ክፍል በተመለከቱ ልዩ ድንጋጌዎች እና ድንጋጌዎቹን መሠረት አድርገው በሚወጡ ደንቦች የሚገዛ ካልሆነ በስተቀር በኢንዱስትሪ ልማት ቀጠናዎች ላይ ይህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈፀም የሚወጡ ደንቦች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## ክፍል ዘጠኝ

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፴፮. ስለብድር እና ስለውጭ ምንዛሬ አጠቃቀም**

፩/ ከውጭ ብድር ያገኘ ባለሀብት ይህንኑ ብድር ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አቅርቦ በባንኩ መመሪያ መሠረት ማስመዝገብ ይኖርበታል።

፪/ ማንኛውም የውጭ ባለሀብት ለኢንቨስትመንት እንቅስቃሴው ዓላማ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በተፈቀዱለት የአገር ውስጥ ባንኮች የውጭ ምንዛሬ የባንክ ሂሣብ መክፈት ይችላል።

c) maintaining natural resources, heritages and places required by law to be preserved.

**35. Regulations Related to Industrial Development Zones**

1/ An organ to engage in the federal government development activities of industrial development zone shall be established by regulation of the Council of Ministers.

2/ Matters concerning designation, allocation standard, boundary delimitation of industrial development zones, the rights and duties of investors engaged in, the services expected from the government and supervision theron, completion of construction activities and supervision thereon,incentives other than those under this Proclamation and the implementation of this Part of the Proclamation, shall be determined by the Council of Ministers regulation.

3/ Unless otherwise it is to be governed by this special Part and regulations based on the provisions of this special Part of this Proclamation, the provision of this Proclamation and regulations issued hereunder shall be applicable to industirial development zones.

## PART NINE

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**36. Loans and Utilization of Foreign Currency**

1/ An investor who acquires an external loan shall have such loan registerd with the National Bank of Ethiopia in accordance with the directive of the Bank.

2/ For the purpose of his investment activities, any foreign investor shall be allowed to open and operate foreign currency accounts in authorized local banks in accordance with directive of the National Bank of Ethiopia.

## ፴፯. የውጭ ዜጎችን ስለመቅጠር

፩/ ማንኛውም ባለሀብት ለሥራው እንቅስቃሴ አስፈላጊ የሆኑና ተገቢው ሙያ ያላቸውን የውጭ አገር ኤክስፐርቶች ሊቀጥር ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የውጭ ዜጎችን የሚቀጥር ባለሀብት ለኢትዮጵያውያን አስፈላጊውን ሥልጠና እንዲሰጥ በማድረግ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የውጭ ዜጎቹ እንዲተኩ የማድረግ ኃላፊነት አለበት።

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ድንጋጌዎች ቢኖሩም የውጭ ባለሀብት ለሚያካሂደው ድርጅት የውጭ ዜግነት ያላቸውን ከፍተኛ የማኔጅመንት አባላት ለመቅጠር ገደብ አይደረግበትም።

## ሌሎች ሕጎችን ስለማክበርና ስለአካባቢ ጥበቃ

ማንኛውም ባለሀብት የአገሪቱን ሕጎች በማክበር የኢንቨስትመንት ተግባሩን ያከናውናል። በተለይም የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ሲያደርግ ለአካባቢ ጥበቃ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ ይኖርበታል።

## ደንብ የማውጣት ሥልጣን

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ማውጣት ይችላል።

## የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

፩/ የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፪፻፹/፲፱፻፺፬ (እንደተሻሻለ) በዚህ አዋጅ ተሽሯል።

፪/ ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

## አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ መስከረም ፯ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

## 37. Employment of Expatriates

1/ Any investor may employ duly qualified expatriate experts required for the operation of his business.

2/ An investor who employs expatriates pursuant to sub-article (1) of this Article, shall be responsible for replacing, within a limited period, such expatriate personnel by Ethiopians by arranging the necessary training thereof.

3/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) and (2) of this Article, a foreign investor shall, without any restriction, have the right to employ expatriate employees on top management positions for his enterprise.

## 38. Duty to Observe Other Laws and Protection of Environment

Any investor shall have the obligation to observe the laws of the country in carrying out his investment activities. In particular, he shall give due regard to environmental protection.

## 39. Power to Issue Regulation

The Council of Ministers may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

## 40. Repealed and Inapplicable Laws

1/ The Investment Proclamation No. 280/2002 (as amended) is hereby repealed.

2/ No law or customary practice shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, have effect with respect to matters provided for in this Proclamation.

## 41. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 17th day of September, 2012.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**